*ጋዜጣዊ መግለጫ*

# በሴት ተማሪዎች የወሊድ ፈቃድ ረቂቅ መመሪያ ዙሪያ የቀረበ የጋራ ጥሪን አስመልክቶ በሴቶች መብት ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

ህዳር 20 ቀን 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# በሴት ተማሪዎች የወሊድ ፈቃድ ረቂቅ መመሪያ ዙሪያ የቀረበ የጋራ ጥሪን አስመልክቶ በሴቶች መብት ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

**ህዳር 20 ቀን 2016 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**

## መግቢያ

እኛ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ሰራተኞችና አባላት ከአጋር የሴቶች መብት ድርጅቶችጋር በመሆን የትብብር ጥሪ እናቀርባለን፡፡ እንደሚታወቀው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የትምህርት ሚኒስቴር በቅርቡ ባወጣው ረቂቅ መመሪያ ክፍል አራት፣ አንቀጽ 15፣ ተራ ቁጥር 5 መሰረት “**አንድ ተማሪ በወሊድ ምክንያት 15 ተከታታይ የትምህርት ቀናት ካረፈች በኋላ ትምህርቷን መቀጠል ትችላለች፣ ሆኖም ግን 16 ቀናትና ከዚያ በላይ ከትምህርት ገበታዋ ከቀረች ከዘመኑ ትምህርት ትታገዳለች፡፡**” የሚል ረቂቅ መመሪያ አውጥቷል፡፡

ይህ ረቂቅ መመሪያ ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ሴቶች የወሊድ ፈቃድ መብትን በእጅጉ የሚገድብ ከመሆኑም በላይ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የተደነገጉትን አወንታዊ የድርጊት ድንጋጌዎች የሚንድና የሴቶችን መሠረታዊ የመማር መብቶች በግልጽ የሚነፍግ ነው፡፡ በተጨማሪም እድል ለመስጠት የተጀመረውን አካታች አካሄድ የሚያደናቅፍና ወደኋላ የሚጎትት አካሄድ ነው፡፡

ልጅ መውለድ በሴቶች ትምህርት ላይ ተደራራቢ ጫና እንደሚፈጥር አጠያያቂ አይደለም፡፡ የወሊድ ፈቃድ መከልከል እና ሴቶች ትምህርታቸውን እንዳይቀጥሉ አማራጮችን መገደብ ደግሞ በሴቶች የትምህርት እንቅስቃሴዎች ላይ ተጨማሪ እንቅፋቶችን መፍጠር ነው፡፡ ይህ ረቂቅ መመሪያም ለሴቶች ሌሎች አማራጮችን ከመፍጠር ይልቅ እንዳይበቁና በህብረተሰቡ ውስጥ ሙሉ በሙሉ መሳተፍ እንዳይችሉ የሚያደርግ ቀጥተኛ ጥቃት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ኢፍትሃዊ እርምጃ ላይ ጠንካራ የውትወታ/ሙግታ ዘመቻ በማድረግና ጫና በመፍጠር እንድትተባበሩንና ከጐናችን እንድትቆሙ ጥሪያችንን እያቀረብን፡ የሚከተለውን ጥያቄ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት አካላት እናቀርባለን፡፡

## 1. ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የትምህርት ሚኒስቴር

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቅርቡ ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ሴቶች የወሊድ ፈቃድ መብትን በእጅጉ የሚገድብ ረቂቅ መመሪያ አውጥቷል። ይህ ረቂቅ መመሪያ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የሴቶች እና የወንዶች እኩልነት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በፖለቲካዊ ዘርፎች፣ ትምህርትን፣ ስራን እና ፍትሃዊ የሀብት ተደራሽነትን እና አስተዳደርን ጨምሮ የሚሰጠውን መብት ተጠቃሚነት በእጅጉ የሚነፍግ ነው።

ሴቶች በዚሁ ሕገ መንግሥት የተደነገጉትን መብቶችና ጥበቃዎች ሲያገኙ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው የሚሉትን እና በእርግዝና እና በወሊድ ምክንያት የሚመጡ ጉዳቶችን ለመከላከል እና ጤናቸውን ለመጠበቅ የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው የሚሉትን እና ሌሎች ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ህጎች የሚጥስና የሚቃረን በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን እንደገና እንዲያጤነውና ከሚመለከታቸው መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ድጋፍ፣ መረጃና ትምህርት በመስጠት በፍጥነት ማስተካከያ እንዲያደርግ ጥሪያችንን አናቀርባለን።

## 2. ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

ህገ መንግስት የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ እና መንግስት በምን አይነት መንገድ እንደሚመሰረት፣ እንደሚመራና እንደሚተዳደር፣ የስልጣን ምንጭ ክፍፍልና የቁጥጥር ሂደትን የሚያመላክት፣ የዜጎችን ጥቅል መብትና ግዴታ የሚተነትን፣ የመንግስት አካላት አደረጃጀት፣ ሀላፊነትና ተግባር የሚያስቀምጥ፣ የህግ አውጪ፣ አስፈጻሚና ተርጓሚ አካላት የሚመሩበትን መርህ የሚያስቀምጥ፣ የመንግስት ቅርጽ ስልጣንና የስልጣን ወሰን የሚዘረዝር፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚዊ ጉዳዮችን የሚዳስስ፣ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚነካና ጥቅል አቅጣጫ የሚያመላክት ነው። ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቅርቡ ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ሴቶች የወሊድ ፈቃድ መብትን በእጅጉ የሚገድብ ረቂቅ መመሪያ አውጥቷል።

ይህ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የሴቶች እና የወንዶች በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በፖለቲካዊ ዘርፎች እኩልነትን የሚጥስ ከመሆኑም በላይ ሴቷ ትምህርትን፣ ስራን፣ የሀብት ተደራሽነትን እና አስተዳደርን የማግኘት መብቷን የሚጥስና የሚቃረን በመሆኑ ጉባኤውም የአገሪቱ የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በተሟላ መንገድ ስራ

ላይ ማዋል አስተማማኝ ዋስትና ሊሰጥ ታምኖበት የተቋቋመ በመሆኑ፤ ይህን ረቂቅ መመሪያ በፍጥነት ማስተካከያ እንዲደረግበት የድርሻውን እንዲወጣ ጥያቄያችንን አናቀርባለን፡፡

## 3. ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ያለው ተቋም እንደመሆ በህገ መንግስት በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቶች የሚያወጡትን ህጎችና መመሪያዎች የመከታተልና የማስፈፀም ስልጣኑን መሰረት በማድረግ ይህ ረቂቅ መመሪያ የሴቶችን ህገመንግስታዊ መብት የሚቃረን፣ የወሊድ ፈቃድ የማግኘትና የመጠቀም መብታቸውን የሚከለክልና ሌሎች ተያያዥ መብቶችን የሚነፍግረቂቅ መመሪያ በመሆኑ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድበት የበኩሉን እንዲወጣ ጥሪያችንን አናቀርባለን፡፡

## 4. ለሚዲያ አካላት በሙሉ

ሚዲያዎች በጎም ሆነ ክፉ ተጽእኖ የመፍጠር ከፍተኛ አቅም ያላቸው እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ረቂቅ መመሪያም የሴቶችን መብቶች የሚንዱና ለሌሎች ተጨማሪ ተግዳሮቶች የሚዳርግ ነው፡፡ ስለሆነም ሚ/ር መ/ቤቱ ጉዳዩን እንደገና እንዲያጤነውና ወደፊትም በሴቶች ላይ መሰል ድርጊቶች እንዳይቀጥሉ ጫና በመፍጠር የሴቶችን ጉዳይ የሁሉም የህ/ሰብ ክፍል ጉዳይ እንዲሆን በማድረግና ጉዳዮችን እስከ መጨረሻው ተከታትሎ ለህዝቡ በማሳወቅ የበኩላችሁን ሚናና ኃላፊነት እንድትወጡ እንጠይቃለን፡፡

## 5. ለሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት

በኢትዮጵያ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጫና የሚፈጥሩ ህጎችና ፖሊሲዎች ሲወጡ ችግሩን ከግምት በማስገባት ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ የውትወታ (advocacy) ስራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል የበኩላችሁን አስተዋጽኦ ታደርጉ ዘንድ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

## 6. ለመላው የህብረተሰብ ክፍል

ሴቶች እንደማንኛውም ዜጎች በህገ መንግስቱ የተደነገገውን የወሊድ ፈቃድ የማግኘትና የመጠቀም፣ የመስራት፣ የመማር፣ ወዘተ… መብት አላቸው፡፡ ስለሆነም ተገቢ ያልሆኑ ምክንያቶችን በመፍጠር ሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የመብት ረገጣዎች ዝም ሊባሉ አይገባም፡፡ ስለሆነም ማንኛውም የህብረተሰብ

ክፍል ሴቶች የወሊድ ፈቃዳቸውን በአግባቡ የመጠቀም መብታቸው እንዲከበር ያገባኛል በማለት የበኩሉን ጥረት እንዲያደርግና ጫና እንዲፈጥር የሴቶች የወሊድ ፈቃድ መብት ረገጣዎችን የማይታገስ ህብረተሰብ እንዲፈጠር እንጠይቃን፡፡

ድርጅቶች ስም

1/ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር

2/ የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት

3/ የኢትዮጵያ ሴቶች መብት ተሟጋች

4/ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ማዕከል

5/ ሴቶች ይችላሉ

6/ የሴቶች ማረፊያ ልማት ማህበር

7/ የኢትዮጵያ ሴቶች የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ጥምረት

8/ ሴታዊት

9/ ሴብድ ቱ ሴቭ

10/ ሲሃ ኔትወርክ

ህዳር 20 ቀን 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ